# አዲስ አበባ

*አዲስ አበባ የህንፃ ኢነርጂ ብቃት ኮድ ፕሮጀክት*



## የፕሮጀክቱ ዳራ

ሲፎርቲ (C40)፣ ከአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን (EPA)፣ እና ኢትዮ ሪሶርስ ግሩፕ (ERG) ጋር በመተባበር ለአዲስ አበባ በዓይነቱ የመጀመሪያውን የህንፃ ኢነርጂ ብቃት (Building energy efficency) ደንብ በጋራ አዘጋጅተዋል። ይህ የቴክኒክ ድጋፍ በከተማው ህንፃዎች ውስጥ ያለ የኢነርጂ አጠቃቀምን በማሻሻል የአየር ብክለት እና የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ያለመ ነው። ዋና ዋና የልቀት ምንጮች ናቸው ተብለው የተለዩ እና ጉልህ የኢነርጂ ብቃት ተግዳሮቶች ያጋጠሟቸው የህንፃ ዓይነቶች ላይ በማነጣጠር ኢነርጂ ቆጣቢ አሰራሮችን እና ከብክለት የጸዱ ታዳሽ ኃይል መፍትሄዎችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ተግባራዊ ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ሲሆን ደንቡ ፀድቆ በሥራ ላይ ሲውል ህንፃዎች ከኢነርጂ ፍጆታ የሚለቁት የአየር በካይ ልቀቶችን እንዲቀንሱ ያስገድዳል፣ ይህም በአጠቃላይ የአየር በካይ ልቀት ቅነሳ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ ያሳድራል። እንዲሁም ለአደገኛ ብክለቶች ያለ ተጋላጭነትን በመቀነስ የህብረተሰቡን ጤናም ያሻሽላል።

## አቀራረብ

1. **ስልታዊ የጥናት ማስረጃዎችን ማዘጋጀት (≈ 6 ወራት)**:
   - ፕሮጀክቱ የከተማውን ኢነርጂ ብቃት አጠቃላይ ገፅታን በመተንተን፣ የህንፃ ኢነርጂ አጠቃቀምን በማጥናት፣ ውጤታማ የፖሊሲ መፍትሄዎችን ለማዘጋጀት የሚስችሉ የኢነርጂ ብቃት ቴክኖሎጂዎችን በመመርመር ፣ ተጽዕኖ ትንተና በማካሄድ፣ እና የኢነርጂ ብቃትን የሚያሻሽሉ ተግባራትን በመለየት ለአየር ጥራት፣ ለህብረተሰብ ጤና እና ኢኮኖሚ የሚሰጡትን ጠቀሜታዎች ገምግሟል። ይህም ጥናት የህንፃ ኢነርጂ ብቃት ደንቡን ለማርቀቅ እንደ ግብዓት ሆኖ አገልግሏል።
2. **የባለድርሻ አካላት ምክክር እና አቅም ግንባታ (≈3 ወራት)**:
   - በስትራቴጂክ የማስረጃ ግኝቶች እና በረቂቅ መመሪያው ላይ ከዚያም ደንቡ ላይ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ለማማከር አራት አውደ ጥናቶች ተካሂዷል።
   - የስትራቴጂክ ጥናታዊ ማስረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እና የፕሮጀክቱን ሂደት እና ግኝቶች ለባለድርሻ አካላት ለማሳወቅ፣ የህዝብ ግንኙነት መመሪያዎች፣ ፖስተሮች እና ብሩቸሮች ተዘጋጅተዋል።
3. **ረቂቅ ደንብ ዝግጅት እና የኦዲት ቅጽ (≈5 ወራት)**:
   - ረቂቅ ደንቡ፣ ከከተማው የደንብ አወቃቀር ቅጽ ጋር የተጣጣመ ነው። የተዘጋጀውን ረቂቅ መመሪያ ለመገምገም እና ለማዳበር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የዘርፉ ተቋማት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሚመራ የቴክኒክ ሥራ ቡድን (TWG) የተቋቋመ ሲሆን በኋላም የቴክኒክ ቡድኑ መመሪያውን ወደ ደንብ ደረጃ ከፍ እንዲል አድርጎ አርቅቆታል።
   - ድንቡን አፀድቆ በስራ ላይ የማዋል ሂደቱን ለመምራት ዝርዝር የጊዜ ሰሌዳ የያዘ የድርጊት መረሀ ግብር ተዘጋጅቷል። ይህም መረሀ ግብር የደንቡን ረቂቅ ማጠናቀቅ፣ በከተማ አስተዳደሩ ፍትህ ቢሮ ማስገምገም፣ ከዚያም ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በማቅረብ ማፀደቅን ያካትታሉ።
   - ደንቡ ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል ጥቅም ላይ የሚውል የኢነርጂ ኦዲት ቅጽ ተዘጋጅቷል፣ ይህም ረቂቅ ደንቡ ተፈጻሚነቱን ማረጋገጥ ያስችላል።

## ውጤቶች

ፕሮጀክቱ የከተማዋን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ የህንፃ ኢነርጂ ብቃት ረቂቅ ደንብ እና ለትግበራ አመቺ ይሆን ዘንድ ዒላማ በተደረጉ ህንጻዎች ላይ የኢነርጂ ብቃት ደንብ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ ከሚያስችል ማስፈጸምያ ቅጽ ጋር አዘጋጅቷል። እንዲሁም በህንፃ ኢነርጂ ብቁነት እና በአየር ጥራት ላይ ግንዛቤ እንዲዳብር፣ በኢነርጂ አጠቃቀም ዙሪያ የነበረ የመረጃ ክፍተቶችን ለመቅረፍ አስችሏል። በተጨማሪም የጥናት ማስረጃዎች በፖሊሲ ነክ ውሳኔዎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚች ማሳየት አስችሏል።

## የተገኙ ትምህርቶች እና የተሰጡ ምክረ ሃሳቦች

በዚህ ፕሮጀክት ከተገኙ ቁልፍ ትምህርቶች ውስጥ አንዱ ባለድርሻ አካላትን በአውደጥናቶች ውስጥ ማሳተፍ እና የቴክኒክ ሥራ ቡድን ማዋቀር የተለያዩ ግባቶችን ለመሰብሰብ እና የተዘጋጀውን የሕንጻ ኢነርጂ ብቃት ደንብ ይዘት በማጎልበት ረገድ እጅግ ውጤታማ መሆኑን ነው። በዚህም ሂደት በመጀመሪያ እንደ መመሪያ የተቀረፀው ኮድ የቴክኒክ ሥራ ቡድኑ አማካኝነት ወደ ደንብ ደረጃ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

የፕሮጀክቱ ትግበራ ካሰገኝው ዋና ምክረ ሃሳቦችም መካከል፤-

1. ለኢነርጂ ሴክተር ባለድርሻ አካላት የረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መተግበር፣
2. የሕንፃ ኢነርጂ ብቃት ደንብን በየጊዜው ማሻሻል፣ መደበኛ የኢነርጂ ኦዲት ማድረግ፣
3. የባለድርሻ አካላትን ትብብር ማጠናከር እና
4. የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች ማካሄድን ያካትታል።

**ለበለጠ መረጃ በዚህ ኢ-ሜል ያግኙን airquality@c40.org**

C40 CITIES